# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ

## ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሬ
ጥ

መጥና
ባዘት

ፈትል

ናና
ብ

ማጠናቀቅ

ም

## ማውጫ


........................................................................................................ 3

........................................................................................... 4

የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሠው ኃይል ............................................................. 5

........................................................................................... 6

የኦዲቱ ዓላማ፤ ......................................................................................... 7

........................................................................................................ 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲትአካባቢ (Potential Audit Area) ........................................... 8

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ......................................................... 8

(Evaluative Criteria) ............................................................................... 9

(Process Description) ............................................................................... 9

........................................................................................................ 12

........................................................................................................ 12

- ........ 12

- ......... 13

- ..................................... 15

........................................................................................................ 16

- ...................................................................................................... 17

- ...................................................................................................... 19

- ................................................................. 21

........... 22

........................................................................................................ 24

......... 25

……………………………………………..27
............................................... 28
............................................... 29
........................................ 30
...................................................................................................................... 33
........................................................................................................................ 33
...................................................................................................................... 36
............................................................................................................. 36
................................................................................................................. 38

1. መካከለኛና ከፍተኛ አቅም ያላቸው የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ከ1930ዎቹ ጀምሮ በአገራችን በመልማት ላይ ያሉ ቢሆንም ረጅም ዘመን የማስቆጠራቸውን ያህል ለአገራችን ኢንዱስትሪ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ ሳያስመዘግቡ ቆይተዋል፡፡ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሀገራችን ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ትኩረት ከተሰጣቸውና ኤክስፖርት መር ከሆኑት ኢንዱስትሪዎች መካከል አንዱ በመሆኑ እና ዘርፉ ካፒታልን በመቆጠብ ሰፊ ጉልበትን የሚጠቀም ሰፊ ገበያ ያለው በመሆኑ ለሀገራችን ዕድገት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ታምኖበት በመስፋፋት ላይ የሚገኝና እየተስፋፋ ያለ ዘርፍ ነው፡፡
2. የአሁኑ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከመቋቋሙ በፊት የዘርፉ ሥራዎች በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስር የጨርቃጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት በሚል በመምሪያ ደረጃ ይከናወን ነበር፡፡ ከዛም በ1994 ዓ.ም ይፋ የተደረገውን የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የጨርቃጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል ያሰፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 125/1998 ተቋቁሞ ነበር፡፡
3. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መንግሥት ለጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ልማት ከሰጠው ልዩ ትኩረት አንፃር ኢንስቲትዩቱ ራሱን ችሎ የተለያዩ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን ለመፈጸም እንዲያስችለው የራሱን ፕሮጀክት ቀርጾ የህንፃ ግንባታው በ1998 ዓ.ም ተጀመረ፡፡ የህንፃ ግንባታውም እንዳለቀ በዘርፉ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ ልማታዊ ባለሀብቶች የሚያስፈልገውን ድጋፍና አገልግሎት በመስጠትና በማሰጠት ለውጤት እንዲበቁ ለማስቻል ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሆነ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/2002 እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡
4. ኢንስቲትዩቱ በማቋቋሚያ ደንቡ የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶችን በሚገባ ለመወጣት እንዲያስችለው በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ዘርፍ የመፍጠር ራዕይን ይዞ በጨርቃጨርቅና ስፌት

ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ዘላቂ (sustainable) የሆነና ኢንዱስትሪው በተፋጠነ መልኩ እንዲስፋፋ ለልማታዊ ባለሀብቱ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ግልፅና ቀልጣፋ አገልግሎትና ድጋፍ የመስጠት ተልዕኮ በመያዝ ሥራ ጀምሯል፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

5. ኢንስቲትዩቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/2002 መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፣

2. ለጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

3. የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፣

4. በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፣

5. የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት ለማሳደግ የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት የስራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፣ ለሠልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፣

6. የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣

7. በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣

8. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር በማድረግ እና በግል ተቋማት መካካልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፣

9. የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎችን ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፣

10. ለጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣

11. የግብዓትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፣

12. ለጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፣

13. ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ሥራን ማከናወን፣

14. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሄዳል እንዲሁም በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፣

15. ለተጠቃሚዎች የሚሠጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፣

16. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደ አግባቡ ክፍያ መጠየቅ፣

17. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣

18. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን

## <u>የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሠው ኃይል</u>

6. የጨርቃጨርቅ ኢንዲስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ በዋና ዳይሬክተር የሚመራ በ7 ዋና የሥራ ሂደቶች እና በ5 ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ነው፡፡ እነሱም የኢንጂነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የሽመናና ሹራብ ስራ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የማጠናቀቂያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣ የጋርመንት ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት እና የግብይት ዳይሬክቶሬት ዋና የሥራ ሂደቶች ናቸው፡፡ የምርምር ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት፣ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፣ የፋይናንስና ሎጂስቲክ ዳይሬክቶሬት፣

የዕቅድና መረጃ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት እና የአሠራር ማሻሻያና የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት በደጋፊ የሥራ ሂደት ውስጥ የተዋቀሩ ናቸው፡፡

7. በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሥር የሚገኙት ሠራተኞች ባላቸው የትምህርት ደረጃ አንፃር ሲገለጹ በሁለተኛ ዲግሪ 10፣ በመጀመሪያ ዲግሪ 79፣ በዲፕሎማና ከዲፕሎማ በታች ያሉ የሠራተኞች ብዛት 79 ናቸው፡፡ በድምሩ 60 ወንድ ባለሙያዎች እና 4 ሴት ባለሙያዎች እንዲሁም 51 ወንድ ድጋፍ ሰጪ እና 53 ሴት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በመዋቅሩ የተፈቀደው የሰው ኃይል 292 ሲሆን አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ግን 168 ናቸው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ፣

8. የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተቀመጠው መሠረት ከመንግስት በሚመደበለት በጀት የሚተዳደር ሲሆን፣ ፕሮጀክቱን ለማስፈፀም እንዲያስችል ደግሞ ከኢትዮጵያ መንግስት 30 በመቶውን ማለትም 57 ሚሊየን ብር፣ ከUNIDO 5.94 ሚሊዮን ብር እና ከተለያዩ ለጋሽ አገራት ማለትም ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ፣ ከጀርመን፣ ከፈረንሣይ፣ ከሆላንድ፣ ከአውስትራሊያ፣ ከጣሊያን፣ ከህንድ እና ከቻይና ከመሳሰሉ ሀገሮች 132 ሚሊዮን ብር እንደሚገኝ ታሳቢ በማድረግ ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ባጠቃላይ 189 ሚሊዮን ብር ተመድቦለታል፡፡

9. የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ሁሉን ችሎ ከተቋቋመበት አመት ማለትም በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመታት የመደበኛ በጀት ብር 5,791,480.00 እና ብር 10,968,083,.52 በቅደም ተከተሉ መሠረት የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 4,780,941.89 እና ብር 8,944,254.30 ወጪ አድርጓል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገለጽ 82.55%፣ እና 81.54% ከተፈቀደለት በጀት የተጠቀመ መሆኑን ያሳያል፡፡ የካፒታል በጀት ለ2003 የተመደበው 32,909,800.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ 18,599,983.71 ነው፡፡ ይህም በፐርሰንት ሲሰላ 56.52% ነው፡፡

10.የጨርቃጨርቅ ኢንዱሰትሪ ልማት ፕሮጀክት ባለፉት አምስት አመታት ማለትም በ1999፣ 2000፣ 2001፣ 2002 እና 2003 ብር 50,651,260.00፣ ብር 129,164,019 ብር 99,079,900፣ ብር25,907,577.97 እና ብር32,909,800.00 የካፒታል በጀት የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 24,583,354.20፣ ብር 112,084,770.00፣ 51,050,573.64፣ 17,078,150.33 እና ብር 10,856,801.69 ወጪ አድርጓል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገለጽ 48.53%፣ 86.78%፣51.52%፣ 65.92% እና 32.99% ከተፈቀደለት የካፒታል በጀት የተጠቀመ መሆኑን ያሳያል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ፤

11.የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የህንፃ ግንባታ ሥራዎች፣ የማሽነሪ ግዥና ተከላ አፈፃፀም እንዲሁም የሚሰጣቸው የድጋፍ ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን በመገምገም በአሰራር ላይ ድክመቶች ከታዩ ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን በመስጠት አሰራሩ እንዲሻሻል ለማድረግ ሲሆን ይህም በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነት ከመወጣት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡በዚሁ መሰረት ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች(Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው::

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ፣

12. ኦዲቱ የሸፈነው ከ1999 ዓ.ምእእስከ 2004 ዓ.ም በጀት ዓመት በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክት የተከናወነውን የሥራ እንቅስቃሴ ነው:: ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆን የኦዲቱ ሥራ ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በተጨማሪ ሥራው በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውን 7 መንግስታዊ እና የግል የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅቶችን የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ እና የአልባሳት ማህበርን እና የባህርዳር ዩንቨርስቲ

የጨርቃ ጨርቅ የፋሽን ዲዛይንና የጋርመንት ፋክልቲን ያካተተ ነው፡፡በዚሁ መሰረት ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመከለስ፣ የመስክ ጉብኝት በማካሄድና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)፣

13. ከላይ የተመለከቱትን የኦዲት ዘዴዎችን በመጠቀም የኦዲት ቡድኑ ለዝርዝር ኦዲቱ የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ለይቷል፡፡ እነሱም የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የህንፃ ግንባታ ሥራዎች፣ የማሽነሪ ግዥና ተከላ አፈፃፀም እንዲሁም የሚሰጣቸው የድጋፍ ሥራዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)፣

14. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት ዓለማ ለማሳካት ለዝርዝር ኦዲቱ ለተለየው የኦዲት አካባቢ ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) አስቀምጧል፡፡ እነርሱም፡-

1. የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የህንፃ ግንባታ ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ መካሄዱን መገምገም፣
2. የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የማሽነሪ ግዥና ተከላ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀሙን መገምገም፣
   - 2.1 የማሽነሪ የግዢ ሂደቱን መገምገም፣
   - 2.2 የማሽነሪዎች የተከላ ሂደቱን መገምገም፣
3. የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚሰጣቸው የድጋፍ ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

15. ተቀመጡትን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ለመመዘን የሚረዱ 46 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅቷል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)፣

16. በኢንስቲትዩቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ ያለው የስራ ሂደት ፍሰት፡-

1. ባለሀብቶችን ወደ ጨርቃ ጨርቅ እና ስፌት ኢንዱስትሪ ዘርፍ እንዲገቡ ማግባባትና መሳብ -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣
2. በውጪ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በጨርቃ ጨርቅ እና ስፌት ኢንዱስትሪ ዘርፍ እንዲገቡ ማግባባትና መሳብ -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣
3. በዘርፉ ታዋቂ የሆኑ የውጪ ሀገር ባለሀብቶችን በማግባባት በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣
4. ስለ ዘርፉ ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማደራጀትና ማሰራጨት መሳብ-በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በእቅድና መረጃ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣
5. በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ-በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ፣
6. በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣
7. የኘሮጀክት ሥራ አመራር ድጋፍ በመስጠት በኘሮጀክት መርሀግብር መሠረት እንዲፈፀም የሎጂስቲክና፣ የጉምሩክ፣ የግንባታ ፈቃድ እና የመሠረተ ልማት መሟላት ድጋፍና ክትትል ማድረግ-በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ፣
8. በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት እንዲያደርጉ ማድረግ -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣
9. ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው የዘርፉ ኢንዱስትሪዎች የፕሮጀክት ፕሮፋይል ማዘጋጀት -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣
10. ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንጅነሪንግ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ድጋፍ ማድረግ -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣

11. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ መረጣ ድርድርና ሽግግር የማማከር ድጋፍ መስጠት -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የጋርመንት ቴክኖሊ.ጅ ስፒኒንግ እና የምርምር ላብራቶሪ ዳይሬክቶሬት ፣

12. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የፕሮጀክት ሥራ አመራር ድጋፍ መስጠት -በኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣

13. ወደ ምርት የተሸጋገረ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ጥራቱ የተጠበቀና አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ የግባት አቅርቦት እንዲያገኙ የማገናኘትና የማስተሳሰር ድጋፍ መስጠት- የግብይት የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

14. በአለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ለማምረት የሚያስችል ደረጃ የማውጣት፣ የፍተሻና የማብቃት ድጋፍ መስጠት- የምርምር ላብራቶሪ፣ የግብይት ፣ የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

15. ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የምርት ጥራትና ምርታማነትን ለመጠበቅ የሚያስችል የማምረቻ መሣሪያዎችን በሙሉ አቅምና በብቃት ሊያንቀሳቅስ የሚችል የቴክኒክ ሥልጠና መስጠት- የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፣

16. ዘመናዊ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ለማደራጀት፣ ለመምራትና የግብይት ሥራን ለማከናወን የሚያስችል አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሥልጠና መስጠት -የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

17. ምርታማነትን ከአለምአቀፍ የምርታማነት ኢንዴክስ ጋር ለማድረስ የሚያስችል የቤንች ማርኪንግ አገልግሎትና ድጋፍ መስጠት -የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣ የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

18. በየወቅቱ የሚፈጠሩ ተስማሚ የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራ ማከናወን -የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

19. የምርምርና ስርጸት ስራዎችን በማከናወን ምርትን ለማልማት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ዲዛይንና ማኑፋክቸሪንግ ሥራዎችን ማከናወንና ማሸጋገር -የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

20. የዘርፉን ሰው ኃይል ክፍተት በመሙላት በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ለማምረት የሚያስችል የክህሎትና የንድፍ ሀሳብ ስልጠና መስጠት -የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣ የሽመና ሹራብ ስራ እና የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ፣

21. ለማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ልማት፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለቤንች ማርክ የሚያገለግሉ ወቅታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በማጠናከር ለባለሀብቶችና ለሌሎች የዘርፉ መረጃ ፈላጊዎች መስጠት - የጋርመንት ቴክኖሎጂ፣የሽመና ሹራብ ስራ ፣ የጥጥ መዳመጫና ፈትል ቴክኖሎጂ እና እቅድና መረጃ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### ለኢንስቲትዩቱ ህንፃ ግንባታ አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት መገለጽን በተመለከተ፡-

17. በሰኔ 2002 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚያወጧቸው ጨረታዎች ላይ የጨረታውን ውጤት በጨረታው ላይ ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች በሙሉ በእኩል ጊዜ በጽሁፍ መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ ለተሸነፉ ተጫራቾች ደግሞ የተሸነፉበትን ምክንያትና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት መግለጽ ይኖርበታል፡፡
18. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ከኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ኢንስቲትዩቱ ባወጣው የህንፃ ግንባታ ጨረታ ላይ በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የተሸነፉበት ምክንያት እና የጨረታው አሸናፊ ማን እንደሆነ በጽሁፍ እንዳልተገለፀ ታውቋል፡፡
19. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በቴክኒካልና ፋይናንሽያል ግምገማ ወቅት ተጫራቾች ለምን እንደተሸነፉ በቃል ተገልጾላቸዋል ፡፡ ስለሆነም ማን እንዳሸነፈ የፋይናንሻል ጨረታው ሲከፈት ተጫራቾች ተጠርተው ስለነበር ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ለተሸናፊ ተጫራቾች በደብዳቤያቸው ላይ ያሸነፈው ተጫራች አለመገለጹ ስህተት እንደሆነ ለኦዲቱ ቡድኑ ገልፀዋል፡፡
20. ኢንስቲትዩቱ ለህንፃ ግንባታ ባወጣው ጨረታ ላይ ተሳታፊ ለነበሩና ለተሸነፉ ተጫራቾች በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት በጨረታው ለተሳተፉት በሙሉ በእኩል ጊዜ በጽሑፍ የተሸነፉበትን ምክንያት እና አሸናፊ የሆነው ተጫራች ማንነት አለመገለጽ በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሊኖር የሚፈለገውን የግልጽነት አሠራር ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ሊያደርግ እና በተጫራች በኩልም በአሠራሩ ላይ እምነት እንዲያጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማዋል የሚያስገነባቸውን ህንፃዎች በተመለከተ፡-

21. ኢንስቲትዮቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስገነባቸው ህንፃዎች በቅድሚያ ጥናት ላይ የተመሠረቱ እና በታቀደው ጊዜ ሳይዘገዩ ቁጠባና ጥራትን መሠረት ባደረገ መልኩ ሊከናወኑ እና ይህንንም ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለው የክትትል እና የቁጥጥር ስራ የሚያካሄድ አማካሪ ድርጅት ሊመደብለት ይገባል፡፡ በግንባታ ሂደትም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወቅታዊ መፍትሔ በመስጠት ኢንስቲትዩቱ ለህንፃ ግንባታው ላወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም /value for money/ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
22. ኢንስቲትዩቱ Northern India Textile Research Association (NITRA) በተባለ የሕንድ ኩባንያ አማካሪነት የቢዝነስ ኘላን ተጠንቶ የተቋቋመ ሲሆን በመጀመሪያ ምዕራፍ እንዲገነቡ የታቀደው ለቢሮ አገልግሎትና ለላብራቶሪ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) ማዕከል እና የስፌት ማዕከልን የሚይዝ ህንፃ ነው፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ለመገንባት የታቀደው የኢንስቲትዩቱ ወርክሾኘ፣ የስልጠና ማዕከል፣ ካፍቴሪያ እና ለሠልጣኖች መኝታ ቤትን ያካተተ ህንፃ ነው፡፡ በሶስተኛ ምዕራፍ ደግሞ ለመገንባት የታቀደው የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮችና አዳራሽን ያካተተ እንደሚሆን በቢዝነስ ኘላኑ ላይ ተገልጿል፡፡
23. ከላይ በተገለፀው የቢዝነስ ኘላን መሠረት ኢንስቲትዩቱ በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት አንድ ግንባታ ለማካሄድ ግሬስ ኢንጂነሪንግ ከተባለ ኮንትራክተር ጋር እ.ኤ.አ በ 7 July 2006 ዓ.ም ብር 39,646,274.17 (በሠላሣ ዘጠኝ ሚሊዩን ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አራት ብር ከአስራ ሰባት ሳንቲም) ውሉ በተፈረመ በአራት መቶ ሰማንያ የካሌንደር ቀን ተጠናቆ ለመረከብ ተዋውሏል፡፡ ይሁን እንጂ ስራው ተጠናቆ ጊዜያዊ ርክክብ የተፈፀመው በውሉ ከተገለፀው በላይ 897 ቀናት የወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በጊዜያዊ የህንፃ ርክክብ ሰነድ ላይ እንደተገለፀው 85 ተጨማሪ ቀናት በvariation ምክንያት፣ተጨማሪ 81 ቀናት በ(time extension) እንደተፈቀደለትና ቀሪዎቹ ቀናት በ21/06/2003 በንግድና ኢንዱስትሪ በተካሄደው ስብሰባ መፈቀዱ ተጠቅሷል፡፡ የህንፃ ግንባታውን በበላይነት የሚቆጣጠረው የኮንስትራክሽን ዲዛይን አ.ማ የኮንትራክተሩን የስራ አፈፃፀም ላይ ጫና የፈጠሩና ግንባታው እንዲዘገይ ምክንያት የሆኑት ጉዳዩች የግንባታ ዕቃዎች በወቅቱ አለማቅረብ፣ ለስራ የሚያስፈልጉትን የሰው

ኃይል በወቅቱ አለማቅረብ በአጠቃላይ በግንባታ ዕቅዱ መሠረት ስራውን አለመስራቱ ለግንባታው መጓተት አስተዋጽኦ ማድረጉን ገልጿል፡፡

24.ኢንስቲትዩቱ በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት ሁለት የህንፃ ግንባታ ለማካሄድ ፖን አፍሪካ ኮንስትራክሽን ኢንጅነርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ እ.ኤ.አ 19 september 2006 ዓ.ም ብር 34,223,399 (በሠላሣ አራት ሚሊዩን ሁለት መቶ ሀያ ሦስት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር) ውሉ በተፈረመ በአራት መቶ የካላንደር ቀናት እንደሚወስድ ታሳቢ በማድረግ የኮንትራት ውል ተፈርሞ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የህንፃ ግንባታው መጠናቀቅ ከነበረበት ከአምስት ዓመት በላይ የፈጀ የግንባታ ስራው እስካሁን ያልተጠናቀቀና ኮንትራክተሩም ስራውን እንዳቋረጠ የኦዲት ቡድኑ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡የሎት ሁለት የህንፃ ግንባታ በታቀደው መልኩ ባለመጠናቀቁና መጓተቱ ለላብራቶሪ ስራዎች ተብለው የተገዙ ዕቃዎች ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ እንዳደረገ በኢንስቲትዩቱ አጠቃላይ የሠራተኞች ስብሰባ ቃለጉባዔ በየካቲት 03 ቀን 2003 ዓ.ም ላይ ተገልጿል፡፡

25.ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኮንትራክተሮቹ በገቡት ውል መሠረት የግንባታ ዕቃዎችን በሚፈለገው መጠንና በተገቢው ጊዜ አቅርቦ ግንባታውን አለማከናወኑ እንዲሁም የቁጥጥሩንና አስተዳደሩን የሚያከናውነው የኮንስትራክሽን ዲዛይን አ.ማ በግንባታ ወቅት ለሚነሱ ጥያቄዎች በተገቢው ጊዜ መልስ ባለመስጠቱና በማዘግየቱ ለግንባታው በወቅቱ አለማለቅ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

26.ስለ ጉዳዩ የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማህበር የአዲስ አበባ ሪጅን ሥራ አስኪያጅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በወቅቱ ግንባታው ሊጠናቀቅ ያልቻለበት ምክንያት በኮንትራክተሩ በኩል የግብአት በወቅቱ አለማቅረብ፣ የውጭ ምንዛሪ ችግር፣ በዋጋ ግሽበትና የህንጻ ተቋራጩ የማኔጅመንት ችግር ሲሆን በእነሱም በኩል አንዳንዱ ጥያቄ ከባድ በመሆኑና በወቅቱ ሳይት ላይ መፍትሄ ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ፣ ሌላው ደግሞ በመስክ ስራ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች ከፍተኛ ፍልሰት ስለነበረ ለቀረቡት ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ ሊሰጡ እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

27.ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሣካት ያስገነባው እና እያስገነባቸው ያሉት ህንፃዎች ውል በተገባበት ጊዜ አለመጠናቀቃቸው ከኢንስቲትዩቱ የሚጠበቀውን

ለኢንዱስትሪው የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማሰልጠንና በዘርፉ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በተሻለ አቅም እንዳይሰጥ ያደረገው ሲሆን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ተገዝተው የመጡ የተለያዩ ማሽኖች እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ እና ለብልሽት እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

## የምዕራፍ ሁለት እና ሶስት የግንባታ ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፡-

28. ኢንስቲትዩቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልጉት በቢዝነስ ኘላኑ ላይ የተገለፁት የምዕራፍ ሁለት እና ሶስት የህንፃ ግንባታዎች በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡

29. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ከኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠየቅ በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት የሚካተቱት የኢንስቲትዩቱ ወርክሾኘ፣ የስልጠና ማዕከል፣ ካፍቴሪያ፣የሠልጣኞች መኝታ ቤት፣ የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮች እና አዳራሽ የግንባታ ስራዎች እንዳልተጀመሩ ታውቋል፡፡

30. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ኘሮጀክቱ ሲቋቋም ጥናቱ የተከናወነው NITRA በሚባል የህንድ ካምፓኒ መሆኑንና የኘሮጀክት ወጪው በመንግስት ይሸፈናል ተብሎ ታስቦ የነበረ መሆኑን፣ አካሄዱ በመንግስት በጀት ላይ ጫና ስለሚያሳድር በየፌዙ እንዲከፋፈሉና እንዲሠሩ የታሰበ እነደነበር ነገር ግን በሂደትና በአሠራር የፌዝ 2 እና የፌዝ 3 በአንድ ላይ በፌዝ 2 እንዲጠቃለሉ አቋም መወሰዱን ገልፀዋል፡፡ይህም በመሆኑም የፌዝ ሁለት ሥራዎች በዚህ ዓመት ለመጀመር በሂደት ላይ መሆኑንና ወደ ቀጣዩቹ ፌዞች ለመሄድ ያልተቻለበት እንደምክንያት የሚጠቀሰው አንደኛ የፌዝ አንድ ሥራዎች ስላልተጠናቀቁ መሆኑ እና ሁለተኛው ደግሞ ወደ ቀጣዩ ፌዝ ለመሄድ ባለመፈለጉ ሌሎችን ስራዎች አዘግይቶ የጋርመንት ዘርፍ በዕድገት ላይ ያለ በመሆኑ ቅድሚያ ለዚህኛው ፌዝ ለመስጠት በማሰብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

31. ኢንስቲትዩቱ በቢዝነስ ኘላኑ ላይ በተገለፀው መሠረት የምዕራፍ ሁለት እና ሦስት የህንፃ ግንባታዎች አለመጀመር ኢንስቲትዩቱ ለሚያካሂደው የስልጠና ስራ በጣም

አስፈላጊ የሆኑት የወርክሾፕ፣የስልጠና ማእከል፣ካፍቴሪያ፣ የሠልጣኞች መኝታ ቤት፣ የመኖሪያ ብሎኮች እና የአዳራሽ ግንባታ እንዳይሟሉ በማድረግ ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን በሚፈለገው ጥራት እና መጠን እንዳያቀርብ አድርጓል፡፡

## የማሽነሪና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ከህንፃ ግንባታዎች ኘሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን በተመለከተ፣

32. ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ከህንፃ ግንባታው ኘሮግራም አፈፃፀም ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፡፡

33. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሠረት ኢንስቲትዩቱ አዲስ በሚያስገነባቸው ህንፃዎች ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው ከውጭ ሀገር የተገዙ የላብራቶሪ መሣሪያዎችና የልብስ ስፌት ማሽኖች ሀገር ውስጥ ቢገቡም የኢንስቲትዩቱ ህንፃ ግንባታ በመጓተቱ ምክንያት መሣሪያዎችን ገጥሞ ስራ ላይ ለማዋል እንዳልተቻለ እና መሣሪያዎቹ ከሁለት ዓመት በላይ ያለስራ እንደተቀመጡ እና የዋስትና ጊዜያቸው እንዳለፈ ታውቋል፡፡

34. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በማንኛውም የኘሮጀክት አተገባበር ወቅት የህንፃ ግንባታና የማሽነሪ ግዢ እንዲጣጣም ተደርጎ ኘሮግራም እንደሚደረግ ሁሉ የህንፃው ግንባታ እና የማሽነሪዎቹ ግዥ ጎን ለጎን ይካሄዳል ተብሎ ታስቦ እንደነበር፣ ይሁን እንጅ የህንፃ ግንባታው በዕቅዱ መሠረት ባለማለቁ ምክንያት ችግሩ ሊከሰት እንደቻለ ገልፀዋል፡፡

35. ኢንስቲትዩቱ ያካሄደው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች የውጭ ሀገር ግዥ የህንፃ ግንባታውን ኘሮግራምና አፈጻጸም ባገናዘበ መልኩ ባለመካሄዱ ኢንስቲትዩቱ ለሚያካሄደው የስልጠናና የምርምር አገልግሎት ላይ ለማዋል የተገዙ ማሽነሪዎች እና መሣሪያዎች ከሁለት ዓመት በላይ ያለስራ እንዲቀመጡና ለብልሽት እንዲጋለጡ እንዲሁም የዋስትና ጊዜያቸውም እንዲያልፍና በዚህ ምክንያት ችግር ቢፈጠር በመንግስት ላይ ተጨማሪ ወጪ ሊያስከትል እንደሚችል ተገንዝበናል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የገዛቸው መሣሪያዎች  እና የላብራቶሪ ዕቃዎች ገጠማ እና የቴክኒክ ምርመራን  በተመለከተ፣

36. ኢንስቲትዩቱ ከአቅራቢ ድርጅቶች የገዛቸውን ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መሣሪያዎች እና የላብራቶሪ ዕቃዎች እንዲቀርቡለት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ባካሄዳቸው የኮንትራት ውል ስምምነቶች መሠረት ድርጅቶቹ ያቀረቡትን መሣሪያዎች የመገጣጠም፣ እንደሚሠራ የማረጋገጥ እና የኮሚሽኒንግ ስራ በኮንትራት ስምምነቱ በተወሰነው ቀን ውስጥ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይገባል። የማሽን ተከላው ከተጠናቀቀ በኋላም ወደ ሥራ ከመገባቱ በፊት የቴክኒክ ምርመራ ማረጋገጫ መስጠት ይኖርበታል።

37. የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ እና ቃለ መጠየቅ መሠረት ኢንስቲትዩቱ ከአቅራቢዎች ጋር ባደረገው የኮንትራት ውል መሠረት የተወሰኑ ዕቃዎች በስምምነቱ መሠረት የቀረቡ ሲሆን የተወሰኑት ግን በኮንትራት መሰረት ያልቀረቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

38. በኢንስቲትዩቱ ለምርመራ ላብራቶሪ ዳይሬክቶሬት የፍተሻ አገልግሎት የሚሰጡ ማሽነሪዎች ግዥን አስመልክቶ አሸናፊ የሆነው ዩሜክ ኢንተርናሽናል ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የUSTER እና TEXT ECHNO MESDAN S.P.A ለምርመራ ላብራቶሪ፣ ለጥጥ መዳመጫ እና ፈትል እና ለሽመናና ሹራብ ክፍል የሚሆኑ መሣሪያዎች መጥተው የተከላ፣ ኮሚሽኒንግ እና ስልጠና ለሠራተኞች የተሰጠ ሲሆን በውሉ መሠረት እንደቀረቡም በገምጋሚ ኮሚቴው ሪፖርት ላይ ተገልጿል።

39. በሌላ መልኩ ኢንስቲትዩቱ ATS ከተባለ ኩባንያ ጋር ባደረገው የጋርመንት መሣሪያዎች እና መለዋወጫዎች የግዥ ኮንትራት ውል መሠረት ዕቃዎቹ ስለመግባታቸው በተካሄደው ግምገማ 184,886.01 ዶላር የሚያወጡ መለዋወጫዎች በኮንትራት ውሉ መሠረት የቀረቡ ሲሆን 20,844.52 ዶላር የሚያወጡ የስፌት መሣሪያ መለዋወጫዎች በኮንትራት ውሉ መሠረት መቅረብ ሲገባቸው እንዳልቀረቡ ታውቋል።ከዚህ በተጨማሪ ብዛታቸው 31 የሆኑ የተለያዩ አይነት መለዋወጫዎች ክፍያ ተፈጽሞ  ከኮንትራት ውሉ ስፔስፊኬሽን ጋር እንደማይጣጣሙ ወደ ግምጃ ቤት ገቢ የሚደረጉ መለዋወጫዎችን በተመለከተ በነሐሴ 30/2003 ዓ.ም በቀረበ ሪፖርት ላይ ተገልጿል።

40.በተመሣሣይ መልኩ ኢንስቲትዩቱ ከግሪን ስታር ኢንተርናሽናል የግል ኩባንያ ለምርምር ላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎች፣ ግላስዌሮች እና ኬሚካሎች ርክክብ ለመፈፀም እቃዎቹ ሲታዩ ጠቅላላ ዋጋቸው 306 ዩሮ የሆኑ 5 ኬሚካሎች በተፈለገው የጥራት መስፈርት ያልቀረቡ፣ ጠቅላላ ዋጋቸው 2971.16 ዩሮ የሆነ ክፍያ የተፈፀመባቸው የአንድ መሣሪያ አካል፣ ሁለት ግላስዌሮች እና 5 ኬሜካሎች ያልቀረቡ መሆኑ፣Ozone Chamber የተባለውን መሳሪያ ተከላ፣ ኮሚሽኒንግ እና ሥልጠና ከጀርመን ሀገር በሚመጣ ባለሙያ ለማከናወን ስምምነት ተደርሶ የሚፈለገው አገልግሎት አለመገኘቱ እንዲሁም Fumming Hood Chamber የተባለው መሣሪያ ተከላ ኮሚሽኒንግ እና ስልጠና ከህንድ አገር በሚመጣ ባለሙያ ለማከናወን ስምምነት ተደርሶ የሚፈለገው አገልግሎት እንዳልተገኘ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ርክክብ ለመፈፀም በተጀመረው ስራ ወኪሉ መሳሪያዎቹ ላይ ምንም ዓይነት ሥልጠና ያላካሄደ በመሆኑ ለተከላ የተከፈለ ክፍያ ሊቀነስ እንደሚገባ ከምርምር ዳይሬክቶሬት በጥር 23/2004 ዓ.ም በቀረበ ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡

41.ስለጉዳዩ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በመስፈርቱ መሰረት ያልቀረቡና በውሉ መሰረት ያልቀረቡ እቃዎች እንዲመለሱ ከአቅራቢዎች ጋር በመጻጻፍና በመደራደር ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ በውሉ መሰረት ኢንስቲትዩቱ ላቅራቢዎች ከመልካም ስራ ዋስትና ማስያዣ በስተቀር ሙሉ በሙሉ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

42.ኢንስቲትዩቱ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መሳሪያዎች እና የላብራቶሪ እቃዎች ግዥን ከአቅራቢዎች ጋር ሲያካሄዱ ATS የተባለው ኩባንያ በኮንትራት ውሉ መሰረት የስፌት መሳሪያ መለዋወጫዎችን አለማቅረቡ፣ብዛታቸው 31 የሆኑ የተለያዩ ዓይነት መለዋወጫዎች ከኮንትራት ውሉ ስፔስፊኬሽን ጋር የማይጣጣሙ መሆኑ፣ከግሪን ስታር ኢንተርናሽናል የግል ኩባንያ ጋር ለምርምር ላብራቶሪ አገልግሎቶች የሚውሉ መሳሪያዎች፣ግላስዌሮች እና ኬሚካሎች የተወሰኑት በተፈለገው የጥራት መስፈርት መሰረት ያልቀረቡ መሆኑ፣ Ozone Chamber እና Fumming Hood Chamber የተባሉት መሳሪያዎች በውሉ መሰረት አቅራቢዎች የመሳሪያ ተከላ ኮሚሽኒንግ እና ስልጠና አለማካሄዳቸው ታውቋል፡፡ ይህም ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የሚያካሄደውን የሰው ሃይል ስልጠናና የድጋፍ አገልግሎት በተሻለ ብቃት እንዳያከናውን ያደርገዋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ለስልጠና አገልግሎት ያስመጣቸውና በትውስት የተሰጡ የልብስ ስፌት መሳሪያዎችን በተመለከተ፣

43. ኢንስቲትዩቱ ለጋርመንት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ስልጠና አገልግሎት ከውጭ ሀገር ያስመጣቸውንና በትውስትና በጊዜያዊነት ለተለያዩ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች የሰጣቸውን የልብስ ስፌት መሳሪያዎች በማሰባሰብ ለኢንዱስትሪው የስልጠና ተደራሽነቱን ማስፋፋት ይጠበቅበታል፡፡

44. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ከስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው 100 የልብስ ስፌት መሳሪያዎችን የአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በትውስት የወሰደ ሲሆን 130 መሳሪዎች ደግሞ በአደይ አበባ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በጊዜያዊነት እንዲቀመጡ በተደረገ ስምምነት የተሰጡ ቢሆንም መሳሪያዎቹ እስካሁን እንዳልተመለሱ ታውቋል፡፡

45. የአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ግንቦት 27 ቀን 1999ዓ.ም በቁጥር አ.ጨ.ጨ ሰ/ማ.ፕ/0007/1999 በተጻፈ ደብዳቤ ለጋርመንት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ስልጠና አገልግሎት የሚውሉ የስፌት ማሽኖች በትውስት ለስድስት ወር ያህል ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ሐምሌ 9 ቀን 1999ዓ.ም በቁጥር 0.1.1..8.2/913 በተጻፈ ደብዳቤ 100 የስፌት መሳሪያዎች በመፈቀዱ ከጨርቃጨርቅ ስፌት ኢንዱስትሪ ኢንስቲትዩት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ጋር የአፈጻጸም ውል በመዋዋል ማሽኖቹን ተረክበዋል፡፡ በውል ስምምነቱ መሰረት ማሽኖቹ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መመለስ ሲኖርባቸው የአልመዳ ጨርቃጨርቅ እያካሄደ የነበረውን የስልጠና አፈጻጸም ለማሳካት ለተወሰነ ጊዜ እንዲራዘምለት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት መግባባት ተደርሶ ተራዝሞለት መቆየቱ ታውቋል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩቱ በትውስት የሰጣቸውን መሳሪያዎች በማሰባሰብ በአጠቃላይ ለኢንዱስትሪው ሴክተር የስልጠና ተደራሽነቱን ለማስፋት በእቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን በመግለጽ በህዳር 3 2003ዓ.ም በንግድና ኢንዱስትሪ ሚንስትር ዴኤታ በተጻፈ ደብዳቤ የስፌት መሳሪያዎቹ እንዲመልሱለት ቢጠየቅም መሳሪዎቹ መመለስ ከሚገባቸው ከሶስት አመት በላይ ያስቆጠሩና እስካሁንም ያልተመለሱ መሆኑ ታውቋል፡፡

46.የኦዲት ቡድኑ በአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በመገኘት የልብስ ስፌት መሳሪያዎቹ ያሉበትን ሁኔታ እና እስካሁን ለኢንስቲትዩቱ ለምን እንዳልተመለሱ ለማጣራት ላቀረበው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ቀደም ሲል ለአልመዳ የሥልጠና ማዕከል የሚጠቅም ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጡ በቁጥር 100 ማሽኖች መኖራቸውንና፣ በአሁኑ ሰዓት የአልመዳ ስልጠና ማዕከል ለተወሰኑ ጊዜያት ተቋርጦ የነበረ በመሆኑ በአንድ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን፣ቢሆንም ንብረቶቹን ለኦዲተሮች ለማሳየት ግን የንብረት ክፍሉን ቁልፍ የያዘ ሰራተኛ እረፍት ላይ በመሆኑ ለማሳየት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም አልመዳ የተጠቀሱትን የልብስ ስፌት ማሽኖች ከአድዋ TVET ጋር በመተባበር ስልጠና ማዕከሉን ለማጠናከርና ንብረቶቹን በስራ ላይ ለማዋል በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ የኦዲት ቡድኑ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው በአካል ተገኝቶ ለማረጋገጥ ያልቻለ ሲሆን የአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካም በውሰት የወሰዳቸውን የልብስ ስፌት መሳሪያዎች ለኢንስቲትዩቱ ለመመለስ እንዳላሰበ የፋብሪካው የሰው ሃይል ኃላፊ በ28/04/2012 በቁጥር 12794/B-2/12 ለፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ኦዲተሮች በጻፉት ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

47.ስለጉዳዩ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ለአልመዳ ልብስ ስፌት 1500 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን በጥያቄ መቅረቡ ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ስለፈቀደ እንደሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ የአደይ አበባ ልብስ ስፌት ፋብሪካ ውስጥ ያሉት ቀሪ 130 የልብስ ስፌት መሳሪያዎች ግን ወደ ኢንስቲትዩቱ ሳይመጡ የቆዩት በኢንስቲትዩቱ መሳሪያዎች የሚገጣጠሙበት ቦታ ተዘጋጅቶ ነገር ግን የኤሌክትሪክ ችግር ያለ በመሆኑ እስካሁን ሳይመጡ የቆዩ መሆኑን፤አሁን ግን ስልጠና በኢንስቲትዩቱ ባለሞያዎች ፋብሪካው ውስጥ እየሰጡባቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

48.ኢንስቲትዩቱ ለጋርመንት ማስፋፊያ ስልጠና አገልግሎት ያስመጣቸውንና በትውስት ለአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሰጣቸው 100 የልብስ ስፌት መሳሪያዎችን በማሰባሰብ ባስገነባው ህንጻ ውስጥ ተክሎ ስራ ላይ አለመዋሉ በዘርፉ የስልጠና እቅድ አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

## የኢንስቲትዩቱ የመረጃ ስርዓትን በተመለከተ፣

49.ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የኢንቨስትመንት ውሳኔ፣ለገበያ ፍለጋ፣ለምርት ግብይት እና ለመሳሰሉት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ በማደራጀት፣ ወደ መረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱም ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ይገባዋል፡፡

50.የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ በአምስት አመት /2003-2007/ መካከለኛና ከፍተኛ የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ላይ ለዘርፉ ኢንቨስትመንት ውሣኔ፣ ለገበያ ፍለጋ፣ ለምርት ግብዓት እና ለመሳሰሉት የሚያገለግል የተሟላና ወቅታዊ መረጃ አለመኖሩ ተገልጿል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የኢንስቲትዩቱን ድረ-ገጽ በማዘጋጀት መረጃዎችን በመረጃ መረብ የማሠራጨት ሥራ አለመከናወኑ ተገልጿል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም የመረጃ ዴስክ ወይም ማዕከል አገልግሎት መስጠት አለመጀመሩና በዘርፉ ዋና ዋና ገዢዎችን በተመለከተ የመረጃ ቋት እንዳላቋቋመ እና ይህም የሆነበት ምክንያት በሰው ኃይልና በኢንፍራስትራክቸር አለመሟላት፣ በኢንስቲትዩቱ የህንፃ ግንባታ አለመጠናቀቅ ምክንያት ወቅታዊ የተሟላና ትክክለኛ መረጃ /የመረጃ ዴስክ/ ማደራጀትና መስጠት አለመቻሉ ተገልጿል፡፡

51.ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ ለሚመለከታቸው 7 የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅቶች ኃላፊዎች ጋር ባካሄደው ቃለመጠይቅ የኒት ቱ ፊኒሽ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ጉምሩክ ጋር ያለውን ችግር ከመፍታት የዘለለ ዋና ዋና የሆኑትን ችግሮቻቸውን የሚፈቱ መረጃዎች ከኢንስቲትዩቱ እንዳልቀረበላቸው ገልጸዋል፡፡ የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ እና የአርባምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ለጥጥ ግዢ የሚያገለግል ከባንክ ጋር በተያያዘ ያለውን ጉዳይ ከማስጨረስ በስተቀር ለገበያ ፍለጋና ለመሳሰሉት ጉዳዮች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከኢንስቲትዩቱ እንዳላገኙ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ አቃቂ የልብስ ሰፌት ፋብሪካ፣ የጉለሌ ስፌት ፋብሪካ፣ ወሲ ጋርመንት እና ዋው ኢንተርናሽናል ፒ ኤል ሲ ለገበያ ፍለጋ፣ ለግብአት አቅርቦት እና ለመሳሰሉት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከኢንስቲትዩቱ እንዳላገኙ ገልጸዋል፡፡

52. ይህንንም በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃለፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ለኢንቨስትመንት የሚያገለግሉ መረጃዎችን በ2003 ለፋብሪካዎች የሰጡት አናሳ እንደሆነ ያረጋገጡ መሆኑን፣ ከ2003 በኂላ ግን በየፈርጁ ጉልህ ሚና ለሚያመጡ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጥያቄዎች ሲቀርቡላቸው መረጃዎችን በተጠናከረ መልኩ እየሰጡ መሆኑን፣ ሆኖም ለሁሉም ባለሃብቶችና ለሌሎች ግን ይህን ማድረግ አለመቻሉን፣ ምክንያቱም ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ በመሆኑና የመረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ደግሞ በጀትና ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህን የመረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ለሚመለከተው አካል የበጀት ጥያቄ ያቀረብን ሲሆን ሲፈቀድላቸው ይህን የመረጃ ስርዓት እንደሚዘረጉ ገልጸዋል፡፡

53. ኢንስቲትዩቱ የመረጃ ስርዓቱን በማጠናከር ለዘርፉ የኢንቨስትመንት ውሳኔ፣ ለገበያ ፍለጋ፣ ለምርት ግብአትና ለመሳሰሉት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማሰባሰብ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የተቀላጠፈ የመረጃ አቅርቦት ስርአት መዘርጋቱ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ በመፍታትና ባለሃብቶቹ በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በኘሮጀክት አፈፃፀም ላይ የሚያደርገውን ክትትልና ድጋፍ በተመለከተ፣

54. ኢንስቲትዩቱ በኘሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

55. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ በዘርፉ ኢንቨስትመንትን በሰፊው ለመሳብ አለመቻል፣ ወደ ኢንቨስትመንት የገቡ ኘሮጀክቶች በብድር፣በመሬትና በመሠረተ ልማት አቅርቦት መጓተት፣ በኮንስትራክሽንና ኮንትራክተሮች አቅም ማነስ እና በመሳሰሉት ችግሮች የተጀመሩት ኘሮጀክቶች በታሰበው ጊዜ መሠረት እንዳልተጠናቀቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በ2003 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ሲ.ኤል.ሲ ኢንዱስትሪ ብድር ለማግኘት የወሰደበት ጊዜ ረጅም መሆኑን፣ ራሱ ኘሮጀክቱ ለባንክ ብድር የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችን በተጠየቀው መሠረት ፈጥኖ ያለማቅረብ፣ የድርጊት መርሀግብሩ ከሚፈለገው ጊዜ በላይ የተለጠጠ መሆኑ፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት አስመልክቶ ችግር ቢያጋጥም ማረጋገጫ እንዲሰጠውና ይህን ከሚመለከተው አካል

ደብዳቤ ለመውሰድ ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ ለስራው የሚያስፈልገውን ጥሬ እቃ ለማቅረብ ከሀገር ውስጥ እጥረት ሲያጋጥመው ከውጭ ለማስገባት እንዲቻል ፈቃድ እንዲሰጠው ፈቃድ ሲጠይቅ ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ በባንኩ በኩል ውሣኔ ለመስጠት ብቃት ማነስ እና ከፍተኛ ክትትል መጠየቅ፣ ተጠንተው የቀረቡ ሰነዶች ለባንክ እንደገና በመታየት ብዙ ጊዜ መውሰዱ ኩባንያው /ኢቱር ቴክስታይል/ የጥናት፣ የሊዝ ውል እና የዲዛይን ሰነዶች በአፋጣኝ ያለማቅረብ፣ የቀረቡትም ቢሆን የተሟላ አለመሆናቸው በፕሮጀክት አፈጻጸም የታዩ ችግሮች መሆናቸው ተገልጿል፡፡

56.የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና ለተመረጡ 7 የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅት የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በመጀመሪያ አካባቢ ላይ በቴክኖሎጂ መረጣ የተለያዩ መረጃዎች የተሰጠው መሆኑን ከዛ በኃላ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ለተከሰቱ ችግሮች መፍትሄ እንዳልተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅና የአዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች  በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ለተከሰቱ ችግሮች ከኢንስቲትዩቱ የተደረገላቸው ድጋፍ አለመኖሩንና ችግሮቹንም በራሳቸው እንደፈቷቸው የገለጹ ሲሆን ችግሮችን በመፍታት በሂደቱም የኢንስቲትዩቱ ምንም እጅ እንደሌለበት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ወሲ ጋርመንት ግቢው ውስጥ ለሚሰራው የማስፋፊያ ፕሮጀክት ኢንስቲትዩቱ ምንም ድጋፍ እንዳላደረገላቸው ገልጸዋል፡፡

57.ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በተለያዩ ምክንያቶች ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ተገቢውን ምላሽ ያልሰጡባቸው ሂደቶች እንዳሉ፣ በባለሃብቶችም ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች ያሉ መሆኑን፣ የአቅም ውስንነትና የሰው ሃይል ክህሎት እጥረት በመኖሩ የተሟላና ወቅታዊ ምላሽ መስጠት እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

58.ኢንስቲትዩቱ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ አለመስጠቱ ዘርፉ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቱን ለማጠናከር አያስችለውም፡፡

**ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የምክርና ድጋፍ ስራ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ፣**

59.ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

60.የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ በአይካ አዲስ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኩባንያ የባንክ ኘሮሰሱን ለማከናወን ከታቀደው ጊዜ በላይ ስለወሰደበት ለማሽነሪና ለግንባታ ማቴሪያል ግዢ የL/C ሂደቶችን መከታተልና መደገፍ፣ መሳሪያዎችን በማጓጓዝ ሂደት ክትትል ማድረግ፣ የማሽን ተከላና ርክክብ ሥራዎችን መከታተልና መደገፍ በሚል የታቀዱ ሥራዎች አለመከናወናቸውን አረጋግጧል፡፡ የአዳማ ፈትል ፋብሪካ የማስፋፊያ ኘሮጀክት ደግሞ የባንክ የብድር ሂደቱ ከታሰበው ጊዜ በላይ በመውሰዱ ምክንያት ኘሮጀክቱ እንደዘገየ ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የSpentex industries አዲስ ኘሮጀክት ደግሞ የባንክ ኘሮሰስ በመዘግየቱ ምክንያት የግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፣ የአጋዥ እና የማምረቻ መሣሪያዎችን ግዥ መፈፀም እና ማጓጓዝ፣ የኘሮጀክቱ የመጀመሪያ ፌዝ የሆነውን እና በቀን 40ቶን ክር ማምረት የሚችለውን ንኤስ የፈትል ፋብሪካ ማሽን ተከላ ማስጀመር ሥራዎች እንዳልተከናወኑ ታውቋል፡፡ የSelenteks textiles አዲስ ኘሮጀክት የኘሮጀክቱ 90 በመቶው በበጀት ዓመቱ እንዲጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም አፈፃፀሙ ሲታይ በከፊል ብቻ እንደተከናወነ ታውቋል፡፡ የEtur textile (Yukesil) አዲስ ኘሮጀክቶች ደግሞ ከግንባታ ማቴሪያሎች ግዢ እስከ ግንባታ ማጠናቀቅ (ማሽን ተከላ መጀመር የመሳሰሉት) የሚሉት ሥራዎች እንዲጠናቀቁና በሰኔ ወር 2003 ዓ.ም ምርት መጀመር ወደ ሚቻልበት ደረጃ መድረስ በእቅዱ የተያዙ ሥራዎች የነበሩ ቢሆንም የባንክ ኘሮሰስ ከታሰበው ጊዜ በላይ በመውሰዱ ምንም አይነት የኘሮጀክት ግንባታም ሆነ የግዢ ሥራ እንዳልተከናወነ ተረጋግጧል፡፡

61.ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ለ7 የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅት ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለመጠይቅ የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ እና የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች በቴክኖሎጂ መረጣ በግንባታና በመሳሰሉት ኢንስቲትዩቱ ምንም አይነት እርዳታ እንዳልሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የወሲ ጋርመንት የቴክኖሎጂ መረጣ በግንባታ በተከላና በሙከራ ምርት በውጪ አገር

በዚሁ ዘርፍ ካሉ ሰዎች ጋር በመመካከር የተሰራ እንደሆነና ኢንስቲትዩቱ ምንም ድጋፍ እንዳላደረገ ገልጸዋል፡፡

62. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የአቅም ውስንነትና የባለሙያ እጥረት የበቃ የሰው ሃይል ችግር በመኖሩ የታሰበውን ማድረግ እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

63. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በግንባታና በተከላ ሂደት ላይ አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ አለማድረጉ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች በፍጥነት ወደ ስራ ገብተው በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዳያሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የሚያስፈልጉትን ተግባር ተኮር ስልጠናዎች መስጠቱን በተመለከተ፣

64. ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ሊያዘጋጅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

65. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ ከመሠረታዊ የልብስ ስፌት ስልጠና ውጪ ሌሎች የስልጠና ዓይነቶች ሊሰጡ እንዳልቻሉ በ2003 የበጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ መገለጹን አረጋግጧል፡፡ ለዚህ ችግር መንስኤ ደግሞ ለስልጠና አገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ ማሽነሪዎች ተተክለው ሥራ አለመጀመራቸው እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ለ120 የጥጥ መዳመጫ እና የፈትል ክፍል ሠራተኞች፣ለ120 የሽመናና የሹራብ ፋብሪካ ክፍል ሠራተኞችና እንዲሁም ለ120 የማጠናቀቂያ ክፍል ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት የስልጠና ፍላጎት ጥናት ተካሄዶና እቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብአቶች እና በሰው ኃይል አለመሟላት ስልጠና ሊሰጥ እንዳልተቻለ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የ2003 የበጀት አመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ኢንስቲትዩቱ መጀመሪያ የውስጥ አቅሙን ስላላደራጀ የፌዴራልና የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ የስልጠና ማዕከሎች በሚሰጡት ስልጠናዎች ላይ ድጋፍ እያደረገ እንዳልሆነ ተገልጿል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ 700 ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑና የምስክር

ወረቀት እንዲሰጣቸው ታቅዶ ስልጠና የሚሰጡ ክፍሎችም መስጠት እንዳልጀመሩ በሪፖርቱ ላይ ተገልጿል፡፡

66.ከዚሁ ጋር በተያየዘ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ተገኝቶ ያነጋገራቸው 7 የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የኒት ቱ ፊኒሽ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ለ30 የስፌት ሰራተኞች ስልጠና ከመስጠት ውጪ ምንም አይነት ተግባር ተኮር ስልጠና ከኢንስቲትዩቱ እንዳልተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከልብስ ስፌት ስልጠና በስተቀር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ማለትም በዊቨንግ በስፒኒንግ ለሱፐርቫይዘሮች ስልጠና እንዳልሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፣ የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ፣ የአርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ፣ የዋው ኢንተርናሽናል ፒ ኤል ሲ እና አምባሳድር ጋርመንት ኢንስቲትዩቱ ለሰራተኞቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ምንም አይነት ስልጠናዎች ተሰጥቷቸው እንደማያውቅ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፊለቀ ጋርመንት ለዋናው ስራ የሚያስፈልግ ስልጠና ማለትም በሰፒኒንግ በዊቪንግ ለሱፐርቫይዘሮች ለቴክኒሺኖች ከኢንስቲትዩቱ እንዳልሰጧቸው ገልጸዋል፡፡ ጂ ኤም ኤም ጋርመንት የተባለው ድርጅት ደግሞ ኢንስትይቱ አጫጭር ስልጠናዎች ማለትም ለኦፕሬተሮች ስልጠና የሰጧቸው ቢሆንም በሌሎች ሙያዎች ላይ ግን ለምሳሌ ለሱፐርቫይዘሮች ለቴክኒሺያኖች የመሳሰሉት ላይ ስልጠና እንዳልሰጣቸው ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

67.ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንቲትዩቱ የሰራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የማሰልጠኛ ክፍሎች ባለመደራጀታቸው መሳሪያዎች ባለመገጠማቸውና ሥልጠናውን ለመስጠት የሚያስችል የሰው ኃይል ባለመኖሩና ስልጠናውን ለመስጠት እንዳልተቻለና ስራውን ለመስራት በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

68.ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የስራ አመራረና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በተጠናከረ መልኩ አለመስጠቱ ዘርፉን በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስስችለውን የስራ ቅልጥፍናና ብቃት እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያፋጥኑ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናቶችን ማካሄዱን በተመለከተ፣

69. ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናትን በማካሄድ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን ሊያግዝና ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትንም ሊደግፍ ይገባል፡፡

70. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ በ2003 የበጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ኢንስቲትዩቱን ከሲትራ ከተባለ ተቋም ጋር በማቀራኘት በኮምቦልቻ፣ ድሬዳዋ እና ክራውን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ላይ የምርጥ ተሞክሮ ጥናት ማካሄድ አስቦ ቁርኝቱ ተግባራዊ ስላልሆነ ስራው እንዳልተሰራ ተገልጿል፡፡ በአዲስ ጋርመንት ፋብሪካ ባለፈው በጀት አመት ለስድስት ወር የተከናወነው የቤንች ማርኪንግ ትግበራው ግምገማ ተከናውኖ ቀሪ ሥራዎችን ለማስተካከል የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ ቀጣይ ትግበራ እንዳልተካሄደ ተገልጿል፡፡

71. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና መርጦ ቃለ መጠይቅ ካደረገላቸው 7 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅቶች መካከል የኒት ቱ ፊኒሽ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የምርጥ ተሞክሮ ጥናት ተሰርቶ እንደነበረ ነገር ግን ውጤታማ እንዳልነበረ ገልጸዋል፡፡ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የአዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣የአርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣የጉለሌ ጋርመንት እና ወሲ ጋርመንት ምርጥ ተሞክሮዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኢንስቲትዩቱ እያገዛቸው እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ ፊለቀ ጋርመንት በሃሳብ ደረጃ ኢንስቲትዩቱ እንዳሳወቃቸው ነገር ግን ተግባራዊ እንዳልተደረገ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዋው ኢንተርናሽናል ፒ ኤል ሲ በኮሚኒኬሽን እጥረት ምክንያት ምርጥ ተሞክሮ በነሱ ድርጅት ላይ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ገልጸዋል፡፡ ይርጋለም አዲስ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ደግሞ የዘርፉን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ተሞክሮዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እስካሁን ከኢንስቲትዩቱ የተደረገላቸው እገዛ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

72. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በ2004 በ13 ፋብሪካዎች ላይ ሊተገበር ታቅዶ በ11 ላይ እየተተገበረ መሆኑን፣ በቀሪዎቹ ላይ ግን ይህን ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑን፣ ምክንያቱም ባለሃብቶቹ

የባለሙያ አቅም ማነስ ችግር ያለባቸው በመሆኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በ2003 ይህ ስራ በፓይለት ደረጃ ብቻ እየተሰራ የነበረ በመሆኑ አብዛኛውን ድርጅቶች ያጠቃለለ እንዳልነበረም ገጸልዋል፡፡

73. ኢንስቲትዩቱ የምርጥ ተሞክሮዎችን ጥናት በተጠናከረ መልኩ በዘርፉ በተሰማሩ ድርጅቶች እንዲተገበር አለማድረጉ የዘርፉን ልማት ካለማፋጠኑም በተጨማሪም በአለም አቀፍ ደረጃ ጥራትን በማጠናከር ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ አያስችልም፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የምርት ፍተሻ የሚያካሂድ መሆኑን በተመለከተ፣

74. ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የፊዚካል የኬሚካልና ኢንቫይሮንምነታል የፍተሻ አገልግሎት በመስጠት የጥራት ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

75. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ በ2003 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው የሎት ሁለት ህንፃ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ለፍተሻ አገልግሎት የተገዙትን መሳሪያዎች ተክሎ ለአገልግሎት ማዘጋጀት አልተቻለም፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ መሣሪያዎችን በተጠናቀቀው ሎት አንድ ህንፃ ላይ በጊዜያዊነት እንዲተከሉ ማድረጉን፣ ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ከሚለቀቁ ፍሳሾች ላይ ናሙና በመሰብሰብ ፍተሻ ለማከናወን እና የመፍትሔ ሃሣብ ለሚመለከተው ክፍል ለማቅረብ በኢንስቲትዩቱ ያለው ላብራቶሪ ተደራጅቶ አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ በመሆኑ ከኢንስቲትዩቱ ውጪ ያሉ ላብራቶሪዎችን ለመጠቀም እንደተገደደና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቀ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

76. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና መርጦ ቃለመጠይቅ ካደረገላቸው 7 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችና የ10 የልብስ ስፌት ድርጅቶች ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የኒት ቱ ፊኒሽ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አዲስ ልብስ ስፌት፣ ጉለሌ ጋርመንት፣ጂ ኤም ኤም ጋርመንት፣ ዋው ኢንተርናሽናል ፒኤል ሲ እና አምባሳድር ጋርመንት የምርት ፍተሻ አገልግሎት ተሰጥቷቸው እንደማውያቅ ገልጸዋል፡፡ በሌላ መልኩ የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በኢንስቲትዩቱ በ 2004 የጥራት ፍተሻ ለማድረግ ሙከራ እየተደረገ

እንደሆነና ከዚህ በፊት ይህ ድጋፍ ተሰጥቷቸው እንደማውያቅ ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

77.ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቱትዩቱ ስራ ኃላፊዎች ላቀረቡት ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በኢንስቲትዩቱ ካሉት የፊዚካል የኬሚካልና የኢንቫይሮንምነታል ላብራቶሪዎች ውስጥ ፍተሻ እያከናወነ ያለው የኪሚካል ላብራቶሪው ብቻ ሲሆን ሌሎች ላብራቶሪዎች ወደ ስራ እንዳይገቡ የላብራቶሪ እቃዎችና መሳሪዎች በሙሉ ርክክብ ያልተፈጸመባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ የህንጻ ግንባታው መዘግየት ምክንያት መሆኑ ተገልጿል፡፡

78.ኢንስቲትዩቱ በጨርቃ ጨርቅና ልብስ ስፌት ኢንዱስትሪዎች የፊዚካል፣ኪሚካልና ኢንቫይሮሜታል የፍተሻ አገልግሎት በተጠናከረ ሁኔታ አለመስጠቱ ዘርፉ ጥራቱን የጠበቀና ተወዳዳሪ ምርት ለገበያ እንዳያቀርብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ከመሄዳቸው በፊት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አዘጋጅቶ መስጠቱን በተመለከተ፣

79.ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ከመሄዳቸው በፊት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታ አዘጋጅቶ ሊሠጣቸው ይገባል፡፡

80.የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ ባለሃብቶች በየዘርፉ ድጋፍ ለማግኘት ከመሄዳቸው በፊት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታ ተዘጋጅቶ እንዳልተሰጣቸው በኢንስቲትዩቱ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ቁጥር 04/2003 ገጽ 8 ላይ ተገልጿል፡፡በተለይ ባለሃብቶች ለስራቸው የሚስፈልጋቸውን ብድር ለማግኘት ማሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር እንደማያውቁ ታውቋል፡፡

81.ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ በመስክ ስራ ቃለመጠይቅ ካቀረበላቸው 7 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅቶች ውስጥ የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ እና የአምባሳድር ጋርመንት ፕሮጀክት ለማስፋፋት ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ኢንስቲትዩቱ አዘጋጅቶ እንዳልሰጣቸው ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡ የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የፕሮጀክት ማስፋፊያውን ሲያካሄዱ ኢንስቲትዩቱ ምንም ድጋፍና አስተዋጽኦ እንዳላደረገ ገልጸዋል፡፡ ወሲ ጋርመንት ድጋፍ ለማግኘት ማሟላት አለብን ብለው ያሏቸውን

ጉዳዮች ቢያሟሉም ኢንስቲትዩቱ ድጋፍ አደረገልን ለማለት አስቸጋሪ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

82.የኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለኢንስትትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ይህን ለማከናወን የአቅም ውስንነት ያለባቸው በመሆኑና ጫና ለመፍጠርም ችግር በመፈጠሩ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

83.ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ድጋፍ ለማግኘት ከመሄዳቸው በፊት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማዘጋጀት እንዲደርሳቸው አለማድረጉ በዘርፉ የሚያጋጥማቸው ችግሮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በመፍታት ባለሃብቶቹ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ አዳዲስ የገበያ ማፈላለግ ስራ ማካሄዱን በተመለከተ፣

84.ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ የውጭ ገበያዎችን በማጥናትና በማስጠናት የተጠናከረ አዳዲስ ገበያ በማፈላለግ የኤክስፖርት ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

85.የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ በተለያዩ የንግድ ትርኢቶች ላይ በመሳተፍ እና የገበያ ጥናት በማድረግ አዳዲስ የገበያ እድሎችን የማግኘትና የማስፋት ልምድ ባለመዳበሩ በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን አማራጭ የገበያ እድሎች መጠቀም ያለመቻል፣ ለገበያ ፍለጋ የሚያገለግል የተሟላና ወቅታዊ መረጃ አለመኖር የመሳሰሉት ችግሮች መኖራቸው አረጋግጧል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለሃብቶች በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆነው ከመገኘት ይልቅ በአንፃሩ ከፍተኛ ጥረት በማይጠይቀው የአገር ውስጥ ገበያ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው፣ የውጪ ገበያን መረጃ ለመሰብሰብ እና ለማሰራጨት የሚያስችሉ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በውጭ አገር አለመኖራቸው ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸው ተገልጿል፡፡

86.በተመሳሳይ መልኩ የአገር ውስጥ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች ከአገር ውስጥ ገበያ ይልቅ ወደ ውጭ ገበያ እንዲያተኩሩ ለማስቻል ከተደረገ ጥናት በማደግ ላይ ካሉ ሀገሮች ምርቶችን እንዲያስገቡ ማበረታታትና ሀገሮቹንም በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከመርዳት አንፃር የአውሮፖ አባል ሀገራት የEBA ህግን

እንዲሁም የአሜሪካ መንግስት የAGOA አጠቃላይ የገበያ ቅድሚያ አሰጣጥ ሥርዓትን (GSP) በዘርፉ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም እ.ኤ.አ በ2007 በአሜሪካ የተሰጠው ከሶስተኛ ወገን የግብአትና ድጋፍ ሰጪ ምርቶችን የማስገባት ፈቃድ ይጠይቅ እንደነበርና በአሜሪካና አፍሪካ ስምምነት መሠረት እስከ 2012 ድረስ የተራዘመ መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ይሁን እንጂ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት የወጪ ምርቶች ላይ የተሰማሩ አምራች ላኪዎቻችን ጨርቅና አክሰሰሪን ከሩቅ ምሥራቅ ሀገሮች የማስመጣት እድላቸው የሚቃጠል በመሆኑ የሀገራችንን የዘርፉን ኢንዱስትሪ እጅግ ሊጐዳው እንደሚችል የአገር ውስጥ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ አምራቾች ምርቶቻቸውን ለአገር ውስጥ ገበያ የበለጠ ትኩረት በመስጠት የማቅረብ ዝንባሌን በመቀየር ወደ ውጪ ገበያ እንዲገቡ ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ በዚሁ ጥናት ተገልጿል፡፡

87. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ በናሙና በተመረጡ 7 የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና 10 የልብስ ስፌት ድርጅቶች ኃላፊዎች ጋር ባካሄደው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የኒት ቱ ፊኒሽ ፋብሪካ ጨርቃጨርቅ፣ ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ አዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ ጉለሌ ጋርመንት እና ወሲ ጋርመንት ኢኒስቲትዩቱ አዳዲስ የውጭ ገበያ በማፈላለግ የድርጅቶቻቸው ኤክስፖርት ስራ ውጤታማ እንዲሆን ኢንስቲትዩቱ  ያደረገላቸው ምንም ድጋፍ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካም ምርቶቻቸውን በሶስት እጥፍ ለማሳደግና ለውጭ አገር ኤክስፖርት ለማድረግ በጣም የሚሰሩበት ወቅት ላይ ቢሆኑም ኢንስቲትዩቱ ይህን አስመልክቶ ምንም ድጋፍ እንዳላደረገላቸው ገልጸዋል፡፡ የአርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካም እስካሁን ድረስ ኢንስቲትዩቱ ምንም የረዳቸው ነገር እንደሌለና አሁን የውጭ ገበያ በራሳቸው ጥረት እንዳገኙ ገልጸዋል፡፡ በተመሰሳይ መልኩ ጂ ኤም ኤም ጋርመንት፣ ዋው ኢንርናሽናል ፒ ኤል ሲ እና ይርጋለም አዲስ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የውጭ ገበያ በማፈላለግ ምንም እርዳታ እንዳላገኙ እና የውጭ ኤክስፖርትን ለማሳደግ የታገዙበት ሁኔታ ባለመኖሩ የተገኘ ውጤት እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

88. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የስራ ክፍሉ የተቋቋመው በ2003 አጋማሽ በኂላ በመሆኑና ከ2003 በፊት በሌሎች የስራ ክፍሎች በተደራቢነትና በተበታተነ መልኩ ስራው ሲሰራ የቆየ በመሆኑ

አጥጋቢ ስራ ተሰርቷል ለማለት እንደሚከብድ ገልጸዋል፡፡ ከ2003 ግማሽ አመት በኋላ ግን ባለሙያ ተቀጥሮ እየተሰራ ቢሆንም የልምድ ውስንነት መኖሩን፣ በተለይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ያለው ባለሃብቱን በመደገፍ ላይ መሆኑን፣ የአደረጃጀት ችግር እና የባለሙያ እጥረት ያለበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

89. ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ የውጭ ገበያዎችን በተጠናከረ መልኩ በማጥናት እና በማስጠናት በዘርፉ ለተሰማሩ ድርጅቶች አዳዲስ ገበያ ባለማፈላለጉ ድርጅቶቹ በአለም አቀፍ ገበያ በመሳተፍ አገሪቱ ልታገኝ ትችል የነበረውን የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ ሊያደርግ እና ባለሃብቶቹም ብዙ ስራ በማይፈልገው በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

- ኢንስቲትዩቱ ባወጣው የህንጻ ግንባታ ጨረታ ላይ በጨረታው ተሳትፈው ለተሸነፉ ተጫራቾች የተሸነፉበት ምክንያት እና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት በጽሑፍ አለመግለጹ፣
- በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት አንድ የህንጻ ግንባታን ለማካሄድ ግሬስ ኢንጅነሪንግ ከተባለ ኮንትራክተር ጋር ባደረገው ስምምነት ስራው ውል በተገባ በአራት መቶ ሰማንያ የካላንደር ቀን ተጠናቆ ለመረከብ ቢዋዋልም ስራው ይጠናቀቃል ከተባለበት ቀን በላይ ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ቀናት ዘግይቶ ጊዜያዊ ርክክብ መፈጸሙ፣
- በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት ሁለት የህንጻ ግንባታ ለማካሄድ ፓን አፍሪካ ኮንስትራክሽን ኢንጅነሪነግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር በ19 September 2006 ዓ.ም. ባደረገው ስምምነት ውል በተገባ በአራት መቶ የካላንደር ቀናት ስራው ተጠናቆ ለመረከብ ቢዋዋልም ስራው መጠናቀቅ ከነበረበት ከአምስት ዓመት በላይ ፈጅቶ የግንባታው ስራ እስካሁን ያልተጠናቀቀና ከኮንትራክተሩ ጋር ያለውም ውል የተቋረጠ መሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ የቢዝነስ ስራ ምዕራፍ ሁለት እና ሶስት የህንጻ ግንባታዎች ውስጥ የተካተቱ የኢንስቲትዩቱ ወርክሾፕ፣ የስልጠና ማእከል፣ ካፍቴሪያ፣ የሰልጣኞች መኝታ ቤት፣የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮች እና አዳራሽ የግንባታ ስራዎች አለመጀመራቸው፣
- አዲስ በሚገነባው ህንጻ እንዲተከሉ ያካሄደው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሳሪያዎች ግዥ የህንጻ ግንባታውን ፕሮግራምና አፈጻጸም ያላገናዘበ መሆኑ፣
- ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የተለያ መሳሪያዎች እና የላብራቶሪ እቃዎች ግዥን ከአቅራቢዎች ጋር ሲያካሄድ ATS የተባለው ኩባንያ በኮንትራክት ውሉ መሰረት የስፔት መሳሪያ መለዋወጫዎችን አለማቅረቡ፣
- ATS የተባለው አቅራቢ ያቀረባቸው 31 የሆኑ የተለያዩ አይነት መለዋወጫዎች ከኮንትራት ውሉ ስፔስፊኬሽን ጋር የማይጣጣሙ መሆኑ፣

❖ ከግሪን ስታር ኢንተርናሽናል የግል ኩባንያ ጋር ለምርምር ላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች፣ግላስዌሮች እና ኬሚካሎች የተወሰኑት በተፈለገው የጥራት መስፈርት ያልቀረቡ መሆኑ፣

❖ Ozone chamber እና Fumming Hood chamber ለተባሉት መሳሪያዎች በውሉ መሰረት አቅራቢዎች የመሳሪያ ተከላ፣ኮሚሽኒንግ እና ስልጠና ያላካሄዱ መሆኑ፣

❖ ለዘርፉ የኢንቨስትመንት ውሳኔ ለገበያ ፍለጋ፣ለምርት ግብይት እና ለመሳሰሉት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣በመተንተን፣በማደራጀት ወደ መረጃ ማዕከል በማስተላለፍ በዘርፉ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች በበቂ ሁኔታ አለማቅረቡ፣

❖ ለጋርመንት ማሰልጠኛ የገዛቸውና በትውስት ለአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሰጣቸው አንድ መቶ የልብስ ስፌት ማሽኖች እንዲሁም 130 መሳሪያዎች በጊዜያዊ ማቆያነት ለአደይ አበባ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሰጣቸውን መመለስ ከሚኖርባቸው ከሶስት አመት በላይ ቢያስቆጥሩም እስካሁን ያልተመለሱ መሆኑ፣

❖ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማደረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ባለመስጠቱ፣ በዘርፉ የተሰማሩ ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ መሰረት ያለመጠናቀቅ፣ ከባንክ ብድር ለማግኘት ለረጅም ጊዜ መውሰድ፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ችግር ሲያጋጥም መፍትሄ ለማግኘት ረጅምጊዜ መውሰድ፣ ለግብዓት የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎችን ከውጭ ለማስገባት ፈቃድ ሲጠየቅ ረጅም ጊዜ መውሰድ፣ በባንክ በኩል በቶሎ ውሳኔ ለመስጠት አለመቻል የመሳሰሉት ችግሮች በዘርፉ መታየታቸው፣

❖ በዘርፉ ለሚሰማሩ እና ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ እየሰጠ ያለው ምክርና ድጋፍ አጥጋቢ አለመሆን፣

❖ የዘርፉን ልማት የሚያግዝና ተወዳደሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የስራአመራርና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በበቂ ሁኔታ አለመስጠቱ፣

❖ የዘርፉን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ጥናትን በማካሄድ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን በበቂ ሁኔታ አለማሳተፉና አለማገዝ፣ ችግሮች መኖራቸውን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ከላይ

የተመለከቱትን ችግሮች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

- ኢንስቲትዩቱ ለህንጻ ግንባታ በሚያወጣው ጨረታ ላይ ተሳታፊ ለነበሩና ለተሸነፉ ተጫራቾች በፌደራል መንግስት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ ላይ በተገለጸው መሰረት በጨረታው ለተሳተፉት በሙሉ በእኩል ጊዜ በጽሁፍ የተሸነፉበትን ምክንያትና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት መግለጽ ይኖርበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስገነባቸው ህንጻዎች በቅድሚያ ጥናት ላይ የተመሰረቱ እና ከታቀደው ጊዜ ሳይዘገዩ ቁጠባና ጥራትን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊከናወን እና ይህንንም ለማሳካት የክትትልና የቁጥጥር ስራን የሚያካሄደው አማካሪ ድርጅት በገባው ውል መሰረት ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር ማካሄዱን በመገምገም፣ በግብአት አቅርቦት፣ በሰው ሃይል እና በሌሎችም አስፈላጊ ሁኔታዎች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዲፈቱ ከፍተኛ ክትትልና በማድረግ ውጤት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ አዲስ በሚያስገነባው ህንጻ እንዲተከሉ የሚካሄደው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሳሪያዎች ግዥ የህንጻ ግንባታውን ፕሮግራምና አፈጻጸም ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ATS ከተባለ ኩባያ ጋር የስፌት መሳሪያዎች እንዲቀርቡለት ባደረገው የኮንትራት ውል መሰረት ያልቀረቡት የመለዋወጫ ዕቃዎች እንዲቀርቡ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ግሪን ስታር ከተባለው ኩባንያ ጋር ባደረገው የኮንትራት ውል መሰረት ለምርምር ላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች፣ ግላስዌሮች እና ኬሚካሎች የተወሰኑት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ መሰረት እንዲቀርቡ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይኖበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ከአቅራቢዎች ጋር ባደረገው የኮንትራት ውል መሰረት Ozone chamber እና FummIng Hood chamber የተባሉት መሳሪያዎች የመሳሪያ ተከላ፣ የኮሚሽኒንግና ስልጠና ስራ እንዲያከናውኑ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ለጋርመንት ማሰልጠኛ የገዛቸውና በትውስት ለአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሰጣቸውን 100 (አንድ መቶ) የልብስ ስፌት ማሽኖችን እና በጊዜያዊ ማቆያነት ለአደይ አበባ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሰጣቸውን 130 (አንድ መቶ ሰላሳ) የልብስ ስፌት ማሽኖች በማሰባሰብ በስልጠና አገልግሎት ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የኢንቨስትመንት ውሳኔ፣ለገበያ ፍለጋ፣ለምርት ግብይት እና ለመሳሰሉት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ በማደራጀት ወደ መረጃ ማዕከል በማስተላለፍ በዘርፉ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች በበቂ ሁኔታ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስትትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ እና ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስትትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የስራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስትትዩቱ የዘርፉን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮችን ጥናት በማካሄድ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን በበቂ ሁኔታ ማሳተፍ ይጠበቅበታል፡፡

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## <u>የኦዲትመመዘኛ መስፈርቶች</u>

የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፣ <u>የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>

የኦዲት ትኩረት አካባቢ፣<u>የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ የህንፃ ግንባታ ሥራዎች፣ የማሽነሪ ግዥና ተከላ አፈፃፀም እንዲሁም የሚሰጣቸው የድጋፍ ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም</u>

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluative Criteria |
|---|---|---|
| 1. | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የህንፃ ግንባታን መገምገም | |
| | | 1.1 ለግንባታው የመነሻ ግምት (engineering estimation) ጥናት ሊኖር ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ (Business plan page) |
| | | 1.2 ለኢንስቲትዩቱ ህንፃ ግንባታ የጨረታው ጥሪ በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳደሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ታትሞ መውጣት አለበት፡፡<br>ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 18) |
| | | 1.3 ኢንስቲትዩቱ ከተጫራቹ የቀረበው የመጨረሻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን ሊገለጽለት ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 46 ቁ.1) |
| | | 1.4 ለተሸነፍ ተጫራቾች የተሸነፉበት ምክንያት እና አሸናፊ የሆነው ተጫራች ማንነት በጽሁፍ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 53) |
| | | 1.5 ኢንስቲትዩቱ ጨረታውን ካሸነፈ ድርጅት ጋር ውል ሲዋዋል የማስረከቢያ ጊዜ፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ ጊዜ፣ የፍተሻ ስነ-ስርዓት እና ዋስትናን በግልጽ ያስቀመጠ ሊሆን ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 25) |
| | | 1.6 ግንባታው ሲያልቅ ከግንባታው የተረፉ ንብረቶች ዋጋቸው ተተምኖ በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ሞ/22 ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፣ የንብረት አስተዳደር) |
| | | 1.7 የግንባታው የጥራት ደረጃ የሚያረጋግጥ አማካሪ ድርጅት መኖር አለበት፡፡<br>(ምንጭ፣ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ውለታ) |
| | | 1.8 ኢንስቲትዩቱ ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር የሚሠራው ሥራ በግልጽ ተቀምጦ ውል ሊፈራረም ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፣ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ውለታ) |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluative Criteria |
|---|---|---|
| | | 1.9 አማካሪው ድርጅት /ባለሙያ/ ሥራው በአግባቡ ካልተወጣ የሚወሰደው እርምጃ በግልጽ በውሉ ላይ ሊኖር ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፣ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ውለታ) |
| | | 1.10 የጽህፈት ቤቱ የህንፃ (Lot 1) ግንባታ ኮንትራቱ በተፈረመ በ480 ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡<br>(Contract Document for Lot 1 Building page 2) |
| | | 1.11 የማሽኖች ተከላ የሚደረግበት የህንፃ (Lot 2) ግንባታ የኮንትራት ውሉ በተፈረመ በ400 ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ (Contract Document for Lot 2 Building page 2) |
| | | 1.12 የኢንስቲትዩቱ የቢሮ አገልግሎት፣ ላብራቶሪ፣ IT ማዕከል፣ የስፌት ማዕከል እና የመሣሡት በቢዝነስ ኘላኑ ላይ በተገለፀው መሠረት ቅድሚያ ተሠጥቷቸው በፌዝ 1 ሊገነቡ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ (Business plan page 332) |
| | | 1.13 የኢንስቲትዩቱ ወርክሾኘ፣ የስልጠና ማዕከል፣ ካፍቴሪያ እና ለሠልጣኞች የዶርሚተሪ ፋሲሊቲዎች በቢዝነስ ኘላኑ ላይ በተገለፀው መሠረት በፌዝ 2 ሊገነቡ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ (Business plan page 332) |
| | | 1.14 የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮችና አዳራሽ በቢዝነስ ኘላኑ ላይ በተገለፀው መሠረት በፌዝ 3 ሊገነቡ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ (Business plan page 332) |
| | | 1.15 ኮንትራክተሩ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የግንባታ ሥራውን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በግልጽ በውሉ ላይ ሊቀመጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 60) |
| | | 1.16 የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ኢንስቲትዩቱ የመቀጫውን መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ እንደሚችል የሚገልጽ አንቀጽ ውሉ እንዲይዝ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 60) |
| 2 | **የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የማሽነሪ ግዥና ተከላ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀሙን መገምገም** | |
| | **2.1 የማሽነሪ የግዢ ሂደቱን መገምገም** | 2.1.1 የማሽነሪ ግዥ ጨረታ ከመውጣቱ በፊት ማሽነሪዎቹ አይነትና የማሽነሪዎቹ ስታንዳርድ የያዘ የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫ ጥናት ሊኖራቸው ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አዋጅ 649 ቁጥር 29 2.1) |
| | | 2.1.2 የማሽነሪ ግዥው በሚከናወንበት ጊዜ ከኢንስቲትዩቱ የሥራ ኘሮግራም ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 14) |
| | | 2.1.3 የማሽነሪ ግዢ የቴክኒክና ፍላጐት መግለጫው |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች Evaluative Criteria |
|---|---|---|
| | | ኢንስቲትዩቱ ሊገዛ የሚፈልገውን እቃ ጥራት/ ጠቀሜታ፣ አሠራርን የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህሪን መሠረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገድብ አድርጐ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 23) |
| | | 2.1.4 የሚዘጋጀው የቴክኒክ መግለጫ የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊውል ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 23) |
| | | 2.1.5 የማሽነሪ ውል በሚገባበት ወቅት የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈፃፀም፣ የርክክብ፣ የፍተሻ ስነ-ሥርዓትእና የዋስትና አተገባበሮች በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ የመግንስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 25) |
| | | **2.1.6 ማሽነሪዎች ከመረከባቸው በፊት በጨረታው /በግዢው/ መስፈርት መሠረት መሆኑን የባለሙያ ማረጋገጫ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡** (ምንጭ፣ ATS, Greenstar, Yomak agreement) |
| | | 2.1.7 ለተገዙ ማሽነሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የአምራች /የሻጭ/ ዋስትና (warranty) ሊኖራቸው ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ ATS, Greenstar, Yomak agreement) |
| | | 2.1.8 ድርጅቶቹ ላስመጧቸው ማሽነሪዎች የmaintenance, operational & spar part ማንዋሎችን በCD እና በሀርድ ኮፒ ከማሽነሪዎች ጋር ተያይዞ መላክ ይኖርበታል፡፡ (ምንጭ፣ ATS, Greenstar, Yomak agreement ተ.ቁ 7 ገጽ 2፣4) |
| | | 2.1.9 ከአቅራቢ ኩባንያዎች የሚላኩ መሣሪያዎች የኮሚሽኒግና የፍተሻ ሥራ ሳይከናወን ክፍያ ሊፈፀም አይገባም፡፡ (Organizational minutes የካቲት 01/2002 ገጽ 6) |
| | | 2.1.10 ከአቅራቢ ኩባንያዎች የሚላኩ መሣሪያዎች የዋስትና መያዣ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ (Organizational minutes የካቲት 01/2002 ገጽ 6) |
| | | 2.1.11 መሣሪያዎችን የሚያስመጡ ድርጅቶች መሣሪያውን የመግጠም ከገጠሙ በኂላ እንደሚሠራ የማረጋገጥ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ሊያደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ፣ Contract agreement ATS,Greenstar &Yomak) |
| | | 2.1.12 ኢንስቲትዩቱ ለመጣው መሣሪያ ያመጣው ድርጅት ቴክኒካል ስልጠና እንዲሠጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፣ Contract agreement ATS,Greenstar &Yomak ተ.ቁ 4) |
| | **2.2 የማሽነሪዎች የተከላ ሂደቱን መገምገም** | 2.2.1 ከአቅራቢው ድርጅት ጋር በተገባው ውል መሠረት ማሽነሪዎቹ በወቅቱ ሊገጠሙ (ሊተከሉ) ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ Organizational minutes የካቲት 03/2003 ተ.ቁ 8) |
| | | 2.2.2 የላብራቶሪ እቃዎች ሳይቱ እንደደረሱ በጽሁፍ ለአቅራቢው ድርጅት ከተገለፀ በኂላ የመገጣጠም፣, እንደሚሰራ ማረጋገጥ እና commissioned በኮንትራት ስምምነቱ በተወሰነው ቀን ውስጥ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ Contract agreement ATS,Greenstar &Yomak) |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች Evaluative Criteria |
|---|---|---|
| | | 2.2.3 የማሽነሪ ተከላ ማንዋል ሊኖረው እና በማንዋሉ መሠረት ሊተከል ይገባል። (ምንጭ፣ Contract agreement ATS,Greenstar &Yomak) |
| | | 2.2.4 ማሽነሪዎች ከመተከላቸው በፊት የጥራት ምርመራ ሊደረግላቸው ይገባል። (ምንጭ፣ Contract agreement ATS,Greenstar &Yomak page 30) |
| | | 2.2.5 የማሽን ተከላው ከተጠናቀቀ በኂላ ወደ ሥራ ከመገባቱ በፊት የቴክኒክ ምርመራ ማረጋገጫ ሊኖር ይገባል። (ምንጭ፣ Contract agreement ATS,Greenstar &Yomak page ) |
| | | 2.2.7 ለተተከሉ ማሽኖች የመድን ዋስትና ሊገባላቸው ይገባል። (ምንጭ፣ የመንግስት የንብረት አስተዳደር ደንብ) |
| | | 2.2.8 የተተከሉ ማሽኖች በኢንስቲትዩቱ በንብረት መዝገብ ሊመዘገቡ ይገባል። (ምንጭ፣ የመንግስት የንብረት አስተዳደር ደንብ) |
| | | 2.2.9 ኢንስቲትዩቱ ያስመጣቸውን የልብስ ስፌት መኪናዎች ወደ ኢንስቲትዩቱ ህንፃ በማሰባሰብ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል። ምንጭ፣ ቃለጉባዔ |
| | | 2.2.10 ተገዝተው የመጡ የልብስ ስፌት መኪናዎች፣ የላብራቶሪ የፍተሻ መሣሪያዎች እና ለማሰልጠኛ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችእስኪተከሉ ድረስ ከብልሽት እና ከስርቆት ለመከላከል በመጠለያ ሊጠበቁ ይገባል። |
| 3 | **የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚሰጣቸው የድጋፍ ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም** | 3.1 ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ወደ መረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱም ለተጠቃሚዎች ሊያሰራጭ ይገባል። (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢን/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.2 ኢንስቲትዩቱ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ሊያደርግ ይገባል። (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢን/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.3 ኢንስቲትዩቱ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሠጥ ይገባል። (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢን/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.4 ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ የምክር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል። (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢን/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.5 ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የማያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ሊያዘጋጅና ሊሰጥ ይገባል። (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢን/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.6 ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናትን |

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች Evaluative Criteria |
| --- | --- | --- |
| | | በማካሄድ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን ሊደግፍ ይገባል፡፡ (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢ/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.7 ኢንስቲትዩቱ ለጨርቃ ጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች ለምርቶች የፍተሻ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ (ምንጭ፣የጨር/ልማ/ኢ/የመቋቋሚያ ደንብ) |
| | | 3.8 ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ከመሄዳቸው በፊት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ አዘጋጅቶ ሊሠጣቸው ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 4/2003 ገጽ 8) |
| | | 3.9 ኢንስቲትዩቱ የውጭ ገበያዎችን በማጥናትና በማስጠናት የተጠናከረ አዳዲስ ገበያ በማፈላለግ የኤክስፖርት ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 4/2003 ገጽ 9) |